የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ምክር ቤት
Ethiopian National Transitional Council

*85 S. Bragg Street, Suite 203*
*Alexandria, VA 22312, USA*
*Tel: 1-571-335-4637*
*www.etntc.org*
*contact@etntc.org*

May 7 2013

# ግልጽ ደብዳቤ ለዶ/ር ቴዎድሮስ አድሃኖም

በ May 5 እለት በዋሽንግተን ዲሲ ከሚተላለፉት ሬድዮኖች በአንዱ ላይ በሰጡት ቃለ-ምልልስ (ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ) የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ም/ቤት (ENTC)፤ የወያኔ-ኢህአዴግ አገዛዝ በተለያዩ አገሮች የሚያደርገውን የአባይ ግድብ ቦንድ ሽያጭ ህጋዊነትን መጠየቁ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ልማት እንደሆነ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በመሰረቱ ትችት የሰነዘሩበትን ኢትዮጵያውያን አሸባሪ እያለ ወህኒ ከሚወረውር ስርዓት ምንም የተለየ ነገር ባንጠብቅም፤ የሚገርመን ነገር ቢኖር ይህ ትምክህተኛ ስርዓት በሀገራችን ውስጥ የሚያደርገውን ህገወጥ ተግባራት በተመሳሳይ በሌሎች ሀገሮች ገብቶ ያንኑ ህግና ስርዓት አልበኝነትና ወንጀለኛነት ለማራመድ የሚሞክር አይን አውጣ መሆኑ ነው።

ዶ/ር አድሃኖም፤ እርስዎና መሰሎችዎ ጥያቄ ያነሳብን ሁሉ ፀረ-ግድብ፤ ፀረ-ኢትዮጵያ፤ ሽብርተኛ ወዘተ ነው እያሉ መለፈፍዎ አዲስ ነገር ባይሆንም ማወቅ ያለብዎት ግን የህግ የበላይነት የሚከበርበት ሀገር ውስጥ ማንም ሰው ምንም አይነት ጥያቄ በህግ ማንሳት እንደሚችልና ጥያቄ በመጠየቁ ወንጀለኛ እንደማይሆን ብቻ ነው። ደግሞስ በስራዎና በድርጅትዎ ስራ የሚተማመኑ ከሆነ ምን ይስፈራዎታል? እርስዎና መሰሎችዎ ለኢትዮጵያ ህዝብ የነፈጉትን ፍትህ አግኝተው ነፃ ይወጣሉ! በአንድ በኩል ወያኔ-ኢህአዴግ ትችቶቹንና ስህተቶቹን በፀጋ የሚቀበል መልዓክ እንደሆነ ይነግሩንና ወድያው እልፍ ብለው በዛው ቃለ-ምልልስዎ ጥያቄ የሚያነሳብኝ ሁሉ የኢትዮጵያ ጠላት ነው ይሉናል። እስቲ የራስዎን ንግግር መልሰው ያዳምጡትና እራስዎን የታዘቡ!

በመሰረቱ ENTC የቦንድ ሽያጭ ህጋዊነትን በተመለከተ ለአሜርካው የገበያ ልውውጥ ኮሚሽን ጥያቄ አቅርቧል። ጥያቄዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

1. በአሜሪካ የሚገኘው የወያኔ-ኢህአዴግ ኤምባሲ ቦንዱን ለመሸጥ ለማንኛውም ህጋዊ የኮሞዲቲ ገበያ ሻጭ ከኮሚሽኑ የሚሰጠውን ፈቃድ አግኝቷል ወይ?
2. ህጋዊ የሽያጭ ፈቃድ ካለው፤ የቦንዱ ሽያጭ የአሜሪካ ዜጎችን ሀብት በማጭበርበር ዘዴ (scam) ለመዝረፍ አለመሆኑን ኮሚሽኑ ምን ማረጋገጫ አግኝቷል?
3. የተሰበሰበዉስ ገንዘብ በምን ላይ እየዋለ ነዉ?

እነዚህን ጥያቄዎች በሚመለከታቸው ክፍሎች እየተከታተልን ስለሆነ ወደፊት የምንደርስበትን ለህዝብ እናሳውቃለን።

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ህዝብ አካልነታችን በራሳችን የደርስንበት መደምደሚያ፤ ይህ የአባይ ግድብ የቦንድ ሽያጭ፤ ወያኔ/ኢህአዴግ ለ 22 አመት ስም እየቀያየረ ለዝርፊያ ከተጠቀመባቸው ዘዴዎች የተለየ እንዳልሆነ በመገንዘብ ህዝቡ እስካሁን እንደሚያደርገው በየሄዱበት እያሳፈረ እንዲመልሳቸው ጥሪ አድርገናል። በተለያዩ ሀገራት ያሉ ኢትዮጵያውያን "ከቦንድ ሽያጭ በፊት መብትና ነጻነት ይከበር፤ ህዝብን ከመኖሪያው ማፈናቀልና የዘር ማጥፋት ወንጀል ይቁም፤ የህሊና እስረኞች ይፈቱ" ወዘተ' እያሉ የሚቃወሙት የሀገርን ልማት ተቃውሞ ሳይሆን በወያኔ-አህአዴግ ላይ ምንም አይነት እምነት ስለሌላቸውና ስርአቱ ዘረኛና ወንጀለኛ መሆኑን በመረዳታቸው ነው። በተመሳሳይ በግዳጅ ከደሞዙ እይተቆረጠና በመዋጮ ዘረፋ እየተዋከበ ያለው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ህዝብም የጥቂት ሰአቶች ነጻነት ቢኖረው ከዚህ ሌላ የሚለው ነገር አይኖርም።

ለመላው ኢትዮጵአውያን ሁሉ፤ ENTC ይህ የዘቀጠ ስርዓት ተወግዶ በምትኩ ሁሉን አቀፍ ሕዝባዊ የሽግግር መንግስት መቋቋም እንዳለበት በፅኑ የሚያምን ህዝባዊ የፖለቲካ ተቋም ነው። ስርአቱን ማስወገድ ብቻ ሳይሆን የሽግግር ስርዓትና ምስረታ ምክክር ውይይትና ቅድመ ዝግጅት ከአሁኑ መጀመር እንዳለበት ያምናል። የዲሞክራሲ ሀይሎች ግለሰቦችና መላው የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል የሚል አካል ሁሉ ተገናኝቶ ይህ የዲሞክራሲያዊ ሽግግር ስርዓት ምን መምሰል እንዳለበት በተጨባጭ ሲያመላክት ብቻ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱን ለመጠየቅ አደባባይ የሚወጣው።

'ትግሉም የጋራ፤ ድሉም የጋራ' በሚል መርህ ተንተርሶ፤ ስራቱን በማስወገድና በመተካት ዙሪያ ENTC በመጪው ጁላይ 2-5 በዋሽንግተን ዲሲ ሁሉን አቀፍ የሽግግር ሂደት ምክክር ጉባኤ አዘጋጅቷል። በዚህ ጉባኤ በአገር ውስጥና በውጭ ያሉ የዲሞክራሲ ሀይሎች፤ የእምነት ተቋማት፤ የሴቶችና የወጣት ማህበራት፤ ታዋቂ ግለሰቦችና ምሁራኖች፤ የመገናኛ ብዙሃንና የአለም አቀፍ ተቋማት ተወካዮች፤ የተጋበዙ ሲሆን በተጨማሪ ጥሪው ያልደረሳቸው ድርጅቶች፤ ቡድኖችና ሀገር ወዳድ ግለሰቦች በ መመዝገቢያው ድህረ-ገፅ በመግባት መመዝገብና የጉባኤው ተሳታፊ መሆን እንደሚችሉ በአንክሮ እናሳስባለን።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ለዘላለም ትኑር!

የኢትዮጵያ ብሄራዊ የሽግግር ም/ቤት (ENTC) አመራር

*ለኮሚሽኑ የተላከውን ደብዳቤ ሙሉ ቃል መመልከት ከፈለጉ እዚህ ይጫኑ*

*የ July 2-5 የሽግግር ምክክር ጉባኤን አጭር መግለጫ እዚህ ያዳምጡ*

*በ July 2-5 ታሪካዊ ጉባኤ ላይ ለመገኘት እዚህ ይመዝገቡ*

*ይህንን ታላቅ ጉባኤ ለማሳካት የበኩልዎን አስተዋጽኦ ለማድረግ እዚህ ይጫኑ*